ቁጥር 714/2003

# ስለመንግስት ሰራተኞች ጡረታ ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

የማህበራዊ ዋስትናን ስርዓት በማስፋፋት ደረጃ በደረጃ ለዜጎች እንዲዳረስ ማድረግ ከአሀገሪቱ ማህበራዊ ፖሊሲ አንዱ አካል ነው ፡፡

የስርዓቱ ተጠናክሮ መቀጠል ለማህበራዊ ፍትህ ፣ለኢንዱስትሪ ሰላም ፣ለድህነት ቅነሳና ለልማት ጉልህ አስተዋጽኦ ስለሚኖረው፤

በስራ ላይ ያለውን የመንግስት ሰራተኞች የጡረታ ዐቅድ አቅም በሚፈቅደው መጠን ማጠናከርና ህጎቹን ማሻሻልና ማጠቃለል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55/1 መሰረት የሚከተለው ታውጇል ፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

   ይህ አዋጅ የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ 714/2003 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

2.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፡-

1. ‹‹የመንግስት ሠራተኛ›› ማለት በመንግስት መስሪያ ቤት በቋሚነት በመቀጠር ደመወዝ እየተከፈለው የሚሰራ ሰው ሲሆን የመንግስት ተሿሚዎችን የምክር ቤት አባላትን እና የመከላከያ ሠራዊትና የፖሊስ አባላትን ይጨምራል ፤
2. ‹‹ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊ ›› ማት ሚኒስቴር ፣ሚኒስቴር ደኤታ፣ምክትል ሚኒስቴር ወይም ተመሳሳይ ደረጃ ያለው የመንግስት ኃላፊ ነው ፤
3. ‹‹የምክር ቤት አባል›› ማለት አፈ-ጉባኤን፣ምክትል አፈ-ጉባኤን እና ማንኛውም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮችምክር ቤት አባልን ያጠቃልላል ፤

4. ‹‹አፈ-ጉባኤ›› ወይም ምክትል ‹‹አፈ-ጉባኤ›› ማለት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም የፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ወይም ምክትል አፈ-ጉባኤ ነው፤

5. ‹‹የመንግስት መስሪያ ቤት›› ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደር መስሪያ ቤት ፣ተቋም ወይም አካል ሲሆን በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ መንግስታዊ ተቋማትና የልማት ድርጅቶችን ይጨምራል፤

6. ‹‹መንግስት›› ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግስት እና የክልል መንግስታትን ያጠቃልላል፤

7. ‹‹ክልል ›› ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 47/1 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬደዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል ፤

8. ‹‹የመከላከያ ሠራዊት አባል›› ማለት በአገር መከላከያ ሠራዊት መተዳደሪያ ሕጎች በቋሚነት ተቀጥሮ ወታደራዊ አገልግሎት የሚሰጥ ማናቸውም ሰው ነው፤

9. ‹‹የፖሊስ አባል›› ማለት በፌደራል ወይም በክልል መንግስት በፖሊስ መተዳደሪያ ሕጎች መሰረት በቋሚነት ተቀጥሮ አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው ነው፤

10. ‹‹ሲቪል መንግስታዊ አገልግሎት›› ማለት በመከላከያ ሠራዊት እና በፖሊስ አባልነት ሳይሆን በሌሎች የመንግስት ሠራተኞች የሚፈጸም አገልግሎት ነው፤

11. ‹‹ወታደራዊ አገልግሎት›› ማለት በአገር መከላከያ ሠራዊት አባላት የሚፈጸም አገልግሎት ነው፤

12. ‹‹የፖሊስ አገልግሎት›› ማለት በፖሊስ አባላት የሚፈጸም አገልግሎት ነው፤

13. ‹‹የልማት ድርጅት›› ማለት የመንግስት የልማት ድርጅቶችንና ከ፶ በመቶ ያላነሰ የካፒታል ድርሻ የመንግስት የሆነባቸውን ድርጅቶችን ያጠቃልላል፤

14. ‹‹አበል›› ማለት የአገልግሎት ጡረታ አበል ፣የጤና ጉድለት ጡረታ አበል፣ የጉዳት ጡረታ አበል ፣ወይም የተተኪዎች ጡረታ አበል ሲሆን የዳረጎት አበልና የጡረታ መዋጮ ተመላሽን ይጨምራል ፤

15 ‹‹ደመወዝ›› ማለት ለስራ ግብርና ለማንኛውም ሌላ ጉዳይ ተቀናሽ የሚሆነው ሂሳብ ሳይነሳለት አንድ ሠራተኛ በመደበኛ የስራ ሰዓት ለሚሰጠው አገልግሎት የሚከፈለው ሙሉ የወር ደመወዝ ነው፤

16. ‹‹ባለመብት›› ማለት በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት አበል የሚያገኝ ወይም አበል ለማግኘት የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ሠራተኛ ወይም ተተኪ ነው፤

17. ‹‹ተተኪ›› ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴/፫ የተዘረዘሩትን ያጠቃልላል፤

18. ‹‹የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ›› ማለት በዚህ አዋጅ ለሚሸፈኑ የመንግስት ሰራተኞች የጡረታ አበል ክፍያና አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ ስርዓት ነው፤

19. ‹‹የጡረታ ፈንዶች›› ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት ለሚሰበሰብ የጡረታ መዋጮና ለሚፈጸም የአበል ክፍያ ተግባር የተቋቋሙ የመንግስት ሠራተኞች የጡረታ ፈንዶች ናቸው፤

20. ‹‹ሰው››ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

21. ‹‹ ኤጀንሲ›› ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 203/2003 የተቋቋመው የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ነው፤

22. በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል፡፡

## 3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

1. የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን የጡረታ ጥቅም የሚመለከተው የአዋጅ ቁጥር 270/1994 ድንጋጌ እና አገሪቱ ተዋዋይ ወገን የሆነባቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ይህ አዋጅ በዜግነት ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የመንግስት ሠራተኞች ተፈጻሚ ይሆናል ፡፡

2. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 52/4 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 653/2001 አንቀጽ 54 መሰረት መብቶቻቸውንና ጥቅሞቻቸውን እንዲያጡ የተደረጉ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችንና የምክር ቤት አባላትን በሚመለከት የዚህ አዋጅ አንቀጽ 19/5 አንቀጽ 20/2 አንቀጽ 21/2 አንቀጽ 22/3 እና አንቀጽ 23/2 ተፈጻሚ አይሆኑም ፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ማህበራዊ ዋስትና ምዝገባና መለያ ቁጥር

4. **ምዝገባ**

1. ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት መስሪያ ቤቱ የተቋቋመበትን ሕግ፣የመንግስት ሠራተኛው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር የሞላውን የህይወት ታሪክ ፣የተሰጠውን የቅጥር ደብዳቤ እና ሌሎች በኤጀንሲው የሚወሰኑ መረጃዎችን ለምዝገባ ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚቀርቡ የምዝገባ መረጃዎች ፡-

ሀ/ ነባር የመንግስት መስሪያ ቤቶችንና የመንግስት ሠራተኞችን የሚመለከቱ ሲሆን ኤጀንሲው በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ፤

ለ/ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን በኋላ የተቋቋመ የመንግስት መስሪያ ቤትን ወይም የተቀጠረ የመንግስት ሰራተኛን የሚመለከት ሲሆን መስሪያ ቤቱ በተቋቋመ ወይም ሠራተኛው በተቀጠረ በ60 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለባቸው ፡፡

5 **.የማህበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር**

1. ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት ሠራተኛ የምዝገባ ማስረጃ ተሟልቶ ሲቀርብ የማህበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር ይሰጠዋል፤ሆኖም የመንግስት መስሪያ ቤቱ ወይም ሰራተኛው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካለው ይኸው ቁጥር የማህበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር ጭምር ሆኖ እንዲያገለግል ይደረጋል ፡፡
2. ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ወደሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ሲዛወር ወይም በሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም በጡረታ ዐቅድ በተሸፈነ የግል ድርጅት ሲቀጠር የማህበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥሩን ለተዛወረበት ወይም ለተቀጠረበት የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የግል ድርጅት የማሳወቅ ግዴታ አለበት ፡፡

6. **የምዝገባ መረጃ ለውጥን ስለማሳወቅ**

1. ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት የራሱንና የመንግስት ሰራተኛውን የምዝገባ መረጃ የሚመለከት ለውጥ ሲያጋጥም ለውጡ ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ በ60 ቀናት ውስጥ የተከሰተውን ለውጥ ከደጋፊ ማስረጃ ጋር አያይዞ ለኤጀንሲው በማቅረብ ማወቅ አለበት ፡፡

2. እያንዳንዱ የመንግስት ሠራተኛ የቤተሰብ ሁኔታን የሚመለከት የመረጃ ለውጥ ሲያጋጥመው ከደጋፊ ማስረጃ ጋር አያይዞ ለኤጀንሲው በማቅረብ ማሳወቅ አለበት ፡፡

3. አበል በመቀበል ላይ የሚገኝ ባለመብት በምዝገባ መረጃው ላይ ለውጥ ሲያጋጥመው ለውጡ ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ በ60 ቀናት ውስጥ ከደጋፊ ማስረጃ ጋር ለኤጀንሲው በማቅረብ ማሳወቅ አለበት ፡፡

4. ማንኛውንም የመንግስት መስሪያ ቤት ፣የመንግስት ሠራተኛ ወይም ባለመብት የሚመለከት የምዝገባ መረጃ ለውጥ ማሳወቂያ ሲቀርብ የማህበራዊ ዋስትና የምዝገባ መለያ ቁጥሩ መጠቀስ አለበት ፡፡

5. የማህበራዊ ዋስትና የምዝገባ መለያ ቁጥር የተሰጠው የመንግስት መስሪያ ቤት በመፍረሱ፣ በመከፋፈሉ ወይም በመቀላቀሉ ምክንያት ሠራተኞቹን እንዲረከብ የተደረገው የመንግስት መስሪያ ቤት በ60 ቀናት ውስጥ ይህንኑ ለኤጀንሲው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት ፡፡

6. የማህበራዊ ዋስትና የምዝገባ መለያ ቁጥር የመንግስት የልማት ድርጅት ወደ ግል ይዞታ ሲዛወር ዝውውሩን ያስፈጸመው መንግስታዊ አካል በ60 ቀናት ውስጥ ይንኑ ለኤጀንሲው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት ፡፡

7. <u>የምዝገባ መረጃን አለማቅረብ የሚያስከትለው ውጤት</u>

1. በዚህ ክፍል በተመለከተው መሰረት የምዝገባ መረጃዎችን አደራጅቶ የማይዝና በወቅቱ ለኤጀንሲው የማያስተላልፍ የመንግስት መስሪያ ቤት የሚመለከተው ኃላፊ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 61 መሰረት ይቀጣል ፡፡

2. በዚህ ክፍል በተመለከተው መሰረት የመረጃ ለውጥን በወቅቱ ለማያቀርብ የመንግስት ሠራተኛ ወይም ባለመብት ለተተኪዎቹ የሚወሰነው አበል አስቀድሞ በኤጀንሲው ተደራጅቶ በተያዘው መረጃ መሰረት ይሆናል ፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ስለጡረታ ዐቅድ፣ፈንዶችና መዋጮዎች</u>

8. <u>ስለ መንግስት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ መቋቋም</u>

የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል ፡

9. <u>ስለጡረታ ፈንዶች መቋቋም</u>

የሚከተሉት የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ ፈንዶች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል ፡፡

1. የሲቪል መንግስታዊ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ
2. የወታደራዊ እና ፖሊስ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ

10. <u>የሲቪል መንግስታዊ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ መዋጮዎች</u>

ለሲቪል መንግስታዊ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ በመንግስት ሠራተኛው ደመወዝ ላይ ተመስርቶ የሚደረገው መዋጮ እንደሚከተለው ይሆናል ፡-

1. በመንግስት መስሪያ ቤቱ 11በመቶ
2. በመንግስት ሠራተኛው 7በመቶ

11. <u>የወታደራዊ እና የፖሊስ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ መዋጮዎች</u>

ለወታደራዊ እና ለፖሊስ አገልግሎት ጡረታ ፈንድ በመንግስት ሠራተኛው ደመወዝ ላይ ተመስርቶ የሚደረገው መዋጮ እንደሚከተለው ይሆናል ፡-

1. በመንግስት መስሪያ ቤቱ 25በመቶ
2. በመንግስት ሠራተኛው 7በመቶ

12. <u>የጡረታ መዋጮ ክፍያ</u>

1. እያንዳንዱ የመንግስት መስሪያ ቤት የሠራተኞቹን የጡረታ መዋጮ ከደመወዛቸው ቀንሶና የራሱን መዋጮ ጨምሮ ለጡረታ ፈንዱ በየወሩ የመክፈል ግዴታ አለበት ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የተገለጸው የጡረታ መዋጮ ለሠራተኞች የወር ደመወዝ ከተከፈለበት ወር መጨረሻ ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ መደረግ አለበት
3. ከሠራተኞቹ ደመወዝ ሊቀነስ የሚገባውን መዋጮ ሳይቀንስ የቀረ የመንግስት መስሪያ ቤት ክፍያውን ራሱ ለመፈጸም ኃላፊ ይሆናል ፡፡
4. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደሩ የፌደራልና የክልል መንግስት መስሪያ ቤቶችና የመንግስት ሠራኞች ጡረታ መዋጮ እንደአግባቡ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና በሚመለከታቸው የክልል አካላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተሰብስቦ በቀጣዩ ወር የመጀመሪያዎቹ የስራ ቀናት ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ይደረጋል ፡፡
5. በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ /ባለ በጀት ያልሆኑ/ የመንግስት መስሪያ ቤቶችና ሠራተኞች ወርሀዊ የጡረታ መዋጮ ኤጀንሲው በሚወክላቸው አካላት አማካኝነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተሰብስቦ በቀጣዩ ወር የመጀመሪያዎቹ  የስራ ቀናት ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ይደረጋል ፡፡

6. ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚሰበስበው የጡረታ መዋጮ በትክክል ገቢ ስለመደረጉ የመቆጣጠር ስልጣን ይኖረዋል ፡፡
7. የክልል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሚፈለግባቸውን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ ገቢ አለማድረጋቸውንና የገንዘቡን መጠን በኤጀንሲው ሲገለጽለት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የፌደራሉ መንግስት ድጎማ ከሚያደርግላቸው በጀት ላይ የመዋጮ ገንዘቡን ቀንሶ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ያደርጋል፡፡
8. ኤጀንሲው ወይም ውክልና የተሰጠው አካል ተገቢውን የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ሳያደርግ ከ3 ወር በላይ የቆየ የመንግስት መስሪያ ቤት መንግስት ከሚመድብለት በጀት ወይም በባንክ ካለው ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ገቢ እንዲሆን የማስደረግ ስልጣን ይኖረዋል ፡፡
9. ማናኛውም ባንክ በኤጀንሲው ወይም ውክልና በተሰጠው አካል ሲጠየቅ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከመንግስት መስሪያ ቤቱ ሂሳብ ላይ ቀንሶ ለኤጀንሲው ወይም ውክልና ለተሰጠው አካል ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት ፡፡
10. በጡረታ ዐቅዱ ለተሸፈኑ ሠራተኞች ደመወዝ የሚከፍል የመንግስት መስሪያ ቤት የባንክ ሂሳቡ የሚገኝበትን የባንክ ቅርንጫፍና የሂሳብ ቁጥሩን ለኤጀንሲው በጽሁፍ የማሳወቅ፣ የባንኩ አድራሻና የሂሳብ ቁጥሩ ሲለወጥም ለውጡ ከተከሰተበት ቀን አንስቶ በ15 ቀናት ውስጥ ለኤጀንሲው በጽሁፍ የመግለጽ ግዴታ አለበት ፡፡
11. ኤጀንሲው ወይም ውክልና የተሰጠው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 መሰረት ሊሰበሰብ ያልቻለን ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ግብር የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ ግብር ከፋዮችን ሀብት በመያዝና በመሸጥ የግብር አሰባሰብ የሚከናወንበትን ስርዓት ለመወሰን የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያወጣውን መመሪያ በመከተል በቀጥታ የመንግስት መስሪያ ቤቱን ንብረት በጨረታ በመሸጥ ገቢ የማስደረግ ስልጣን ይኖረዋል
12. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 7 መሰረት የሚወሰነው የጡረታ አበል በጡረታ ፈንድ ላይ ለሚያስከትለው ተጽዕኖ የመንግስት ሰራተኛው በህጉ መሰረት ጡረታ ለመውጣት ለሚቀረው ጊዜ በየወሩ ሊከፈል የሚገባው የጡረታ መዋጮ ታስቦ በቅድሚያ በመንግስት መስሪያ ቤቱ ገቢ መደረግ አለበት ፡፡
13. ከኃላፊነት ለተነሱ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችና የምክር ቤት አባላት የሚከፈለው የጡረታ አበል በጡረታ ፈንድ ላይ ለሚያስከትለው ተጽዕኖ የጡረታ መውጫ ዕድሜ

ለመድረስ ለሚቀረው ጊዜ በየወሩ ሊከፈል የሚገባው የጡረታ መዋጮ ታስቦ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለጡረታ ፈንዱ በቅድሚያ ገቢ መደረግ አለበት ፡፡

14. ከጡረታ መዋጮ ገንዘብ ላይ ቀንሶ ለ፤አገልግሎት ክፍያ፣ ገንዘብ ለማስተላለፊያ ፣ለዕዳ መክፈያ ወይም ለማንኛውም አገልግሎት መጠቀም የተከለከለ ነው ፡፡

15.ኤጀንሲው የጡረታ መዋጮ ገቢን ከመሰብሰብና ከማስፈጸም ጋር የተያያዙ ማናቸውንም ስራዎች ለሌሎች አካላት ውክልና በመስጠት ማሰራት ይችላል ፡፡

16.የጡረታ መዋጮ ክፍያ ከማንኛውም ዕዳ ክፍያ ቅድሚያ ይኖረዋል ፡፡

## 13. <u>የጡረታ ፈንዶች አስተዳደር</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 የተቋቋሙትን የጡረታ ፈንዶች የሚያስተዳድረው ኤጀንሲው ይሆናል

## 14. <u>የጡረታ ፈንዶች አጠቃቀም</u>

1. የጡረታ ፈንዶቹ ጥቅም ላይ የሚውሉት ፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን የጡረታ አበል ክፍያዎች ለመፈጸም ፤

ለ/ ለትሬዠሪ ቦንድ መግዣና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ለሚወሰኑ ሌሎች አትራፊና አስተማማኝ ኢንቬስትመንቶች ፤እና

ሐ/ ለኤጀንሲው አስተዳደራዊ ወጪዎች ብቻ ይሆናል ፡፡

2. የጡረታ ፈንዶች በማናቸውም የዕዳ ክፍያ ምክንያት ሊከበሩ ወይም ሊያዙ አይችሉም ፡፡

## 15. <u>የአክቹዋሪ ግምገማ</u>

የመንግስት ሠራተኞች የጡረታ ዐቅድ በየአምስት ዓመቱ በሂሳብ ስሌት ባለሙያዎች እንዲገመገም ይደረጋል ፡፡

# <u>ክፍል አራት</u>

# <u>ስለአገልግሎት ዘመንና የጡረታ መውጫ ዕድሜ</u>

## 16. <u>የአገልግሎት ዘመን መቆጠር ስለሚጀምርበት ጊዜ</u>

1. የመንግስት ሠራተኛ የአገልግሎት ዘመን መቆጠር የሚጀምረው በመንግስት ሰራተኝነት ከተቀጠረበት ወይም ከተመደበበት ቀን አንስቶ ነው ፡፡

2. ወደ መንግስት ይዞታ በተዛወረ ድርጅት ውስጥ የሚሰራ የመንግስት ሰራተኛ በዚህ አዋጅ ድንጋጌ መሰረት የሚከፈለውን የጡረታ መዋጮ ሊሸፍን የሚችል ፕሮቪደንት ፈንድ ያለው ከሆነ ገንዘቡ ሙሉ በሙሉ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ሆኖ መዋጮ መከፈል

ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ያለው አገልግሎት ይያዝለታል ፤ ሆኖም የፕሮቪደንት ፈንድ የሌለው ከሆነ ድርጅቱ ወደ መንግስት ከተዛወረበት ጊዜ አንስቶ አገልግሎቱ ይያዝለታል ።

3. የመንግስት ሠራተኛው በግል ድርጅቶች ሰራተኞች የጠረታ ዐቅድ በሚሸፈን የግል ድርጅት የፈጸመው አገልግሎት በዐቅዱ መዋጮ መክፈል ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ይያዝለታል ።ለዚህ አገልግሎት አያያዝ የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድን የሚያስተዳድረው አካል የሠራተኛውን የግል መረጃና በግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ የተከፈለውን የጡረታ መዋጮ ገንዘብ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለመንግስት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ ማዛወር አለበት።

## 17. የአገልግሎት ዘመን አያያዝ

1. የአገልግሎት ዘመን የሚቆጠረው በሙሉ ዓመታት፣ በወራትና በቀናት ታስቦ ነው ።

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ ሽፋን ባለው ድርጅት የፈጸመው የአገልግሎት ዘመን በሙሉ ተዳምሮ ይታሰባል ።

3. ለማንኛውም የመንግስት ሠራተኛየሚከተለው አገልግሎቱ ይታሰብለታል ፦

ሀ/ ከጡረታ ዕድሜ መውጫ በኂላ አገልግሎቱ በሕግ መሰረት ተራዝሞለት በስራ ላይ እንዲቆይ የተደረገበት ጊዜ፤

ለ/ የጡረታ መውጫ ዕድሜው በመድረሱ አበል ከተወሰነለት በኂላ በመንግስት ውሳኔ ወደ ስራ ተመልሶ አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፤

ሐ/ የደመወዝ ክፍያ ሳይቋረጥ በማናቸውም ምክንያት አገልግሎቱ ተቋርጦ የቆየበት ጊዜ ፤

መ/ በየወሩ ደመወዝ እየተከፈለው ሙሉ ጊዜውን በማናቸውም የመንግስት አካል ወይም በሰራተኛ ማህበር በተመራጭነት አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፤

ሠ/ በቋሚነት በተቀጠረበት የመንግስት መስሪያ ቤት በጊዜያዊነት ሳያቋርጥ በተከታታይ አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፤

ረ/ በመንግስት ትዕዛዝ መንግስት ከ50 በመቶ በታች የካፒታል ድርሻ በያዘበት ድርጅት በማገልገል ያሳለፈው ጊዜ፤

ሰ/ በመንግስት ውሳኔ በዓለም አቀፍ ድርጅት በማገልገል ያሳለፈው ጊዜ

ሸ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /4/ሀ/ የተደነገገው ቢኖርም ከጡረታ መውጫ ዕድሜ በኋላ በምክር ቤት አባልነት አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፤

4. ለማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ በዚህ አንቀጽ መሰረት ለሚያዝለት የአገልግሎት ዘመን የሚከተለው አይታሰብለትም ፡-

ሀ/ አገልግሎቱ በህጉ መሰረት ካልተራዘመ በስተቀር የጡረታ መውጫ ዕድሜው ከደረሰበት ከሚቀጥለው ወር አንስቶየሚሰጠው አገልግሎት፤

ለ/ ኢትዮጵያ ተዋዋይ ወገን የሆነችበት ማናቸውም ዓለም አቀፍ ስምምነትና የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ /ሠ/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በሕጋዊ ፈቃድ የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነ የመንግስት ሠራተኛ የኢትዮጵያን ዜግነት ከማግኘቱ በፊት በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም በጡረታ ዐቅድ በተሸፈነ የግል ድርጅት የሰጠው አገልግሎት፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከፊደል ተራ (ሐ) እስከ (ሸ) የተመለከተው ጊዜ በአገልግሎት ዘመንነት ሊታሰብ የሚችለው ሠራተኛው ወይም ተመራጩ መክፈል ያለበትን የጡረታ መዋጮ የአሰሪውን ድርሻ ጨምሮ ራሱ የከፈለ ወይም እንዲከፈልለት ያደረገ እንደሆነ ነው ፡፡

6. በዚህ አዋጅ ወይም በግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ መሰረት ዳረጎት ተከፍሎት ወይም መዋጮ ተመላሽ ተደርጎለት የነበረ ሰው እንደገና በመንግስት ሠራተኝነት የተቀጠረ ወይም የተመደበ ከሆነና የወሰደውን ዳረጎት ወይም መዋጮ ተመላሽ ከባንክ የማስቀመጫ ወለድ ጋር መልሶ ገቢ ካደረገ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 16/3 እንደተጠበቀ ሆኖ የቀድሞው አገልግሎቱ ይታሰብለታል፡፡

7. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ኤጀንሲው በሚያቀርብለት ጥናት መሰረት በከባድ ወይም ለጤንነትና ለሕይወት አስጊ በሆኑ የስራ መስኮች የተፈጸመ አገልግሎት እስከ አጠፌታ እንዲቆጠር ሊወስን ይችላል ፡፡

18. <u>የጡረታ መውጫ ዕድሜ</u>

1. የጡረታ መውጫ ዕድሜ የመንግስት ሠራተኛው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር በቅድሚያ የመዘገበውን የልደት ዘመን መሰረት በማድረግ እንደሚከተለው ይሆናል ፡-

ሀ/ ለመከላከያ ሠራዊት አባላት በሠራዊቱ መተዳደሪያ ህግ በሚወሰን ዕድሜ፤

ለ/ ለፖሊስ አባላት በፖሊስ መተዳደሪያ ህግ በሚወሰን ዕድሜ፤

ሐ/ ለሌሎች የመንግስት ሠራተኞች 60 ዓመት፤

2. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ኤጀንሲው በሚያቀርብለት ጥናት መሰረት በልዩ ሁኔታ ለሚታዩ የሙያ መስኮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) ከተመለከተው በላይ የሆነ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ሊወስን ይችላል፡፡
3. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ኤጀንሲው በሚያቀርብለት ጥናት መሰረት በከባድ ወይም ለጤንነትና ለህይወት አስጊ በሆኑ የስራ መስኮች ላይ ለተሰማሩ የመንግስት ሠራተኞች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከተው ያነሰ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ሊወስን ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለአገልግሎት ጡረታ አበልና ዳረጎት

### 19. የአገልግሎት ጡረታ አበል

1. ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ የመንግስት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜው በመድረሱ ከስራ ሲሰናበት የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል ፡፡
2. ቢያንስ 20 ዓመት ያገለገለ የመንግስት ሠራተኛ በራሱ ፈቃድ ወይም በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጭ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል ስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል ፡፡
3. ቢያንስ 25 ዓመት ያገለገለ የመንግስት ሠራተኛ በራሱ ፈቃድ ወይም በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጭ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሊደርስ አምስት ዓመት ከሚቀረው ጊዜ ጀምሮ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል ፡፡
4. ዕድሜው ለጡረታ ሲደርስ የጡረታ መብት መከበሩ እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ድንጋጌ በዲስፕሊን ጉድለት ምክንያት አገልግሎቱ ለተቋረጠ የመንግስት ሠራተኛ ተፈጻሚ አይሆንም ፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ቢያንስ አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያገለገለ አንድ የመንግስት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል ከኃላፊነት ሲነሣ ዕድሜው 50 ዓመት የሞላው ከሆነ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል ፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) ወይም (3) ወይም (4) መሰረት አገልግሎቱ የተቋረጠ የመንግስት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሳይደርስ በጤና ጉድለት ምክንያት ለስራ ብቁ አለሞኑ ከተረጋገጠ ይኸው ከተረጋገጠበት ጊዜ ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል ፡፡የሞተ እንደሆንም ከሞተበት ጊዜ ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ ለተተኪዎች አበል ይከፈላል ፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የመንግስት መስሪያ ቤቱ ህልውና በማክተሙ ፤የሰው ኃይል ብዛቱ ከሚፈለገው በላይ በመሆኑ ወይም ከፕራይቬታይዜሽን ጋር በተያያዘ ከስራ እንዲሰናበት ከተደረገና አገልግሎቱ ከ25 ዓመት ያላነሰና ዕድሜው ከ50 ዓመት ያላነሰ ከሆነ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲወሰን የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል ፡፡

20.<u>የአገልግሎት ጡረታ አበል</u>

1. ለማንኛውም 10 ዓመት ላገለገለ የመንግስት ሰራተኛ የሚከፈለው የአገልግሎት ጡረታ አበል መጨረሻ ባገለገለባቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ ይከፈለው የነበረው አማካይ ደመወዝ 30 በመቶ ሆኖ ከ10 ዓመት በላይ ለፈጸመው ለእያንዳንዱ ዓመት አገልግሎት፡-

   ሀ/ የመከላከያ ሠራዊት ወይም የፖሊስ አባል ላልሆነ የመንግስት ሰራተኛ 1.25 በመቶ ይሆናል፤

   ለ/ ለመከላከያ ሠራዊት ወይም ለፖሊስ አባል 1.65 በመቶ ተጨምሮ ይታሰባል ፡፡
2. ቢያንስ አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ላገለገለ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል መጨረሻ ባገለገለባቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ ይከፈለው የነበረው አማካይ ደመወዝ 15 በመቶ ፤ ከአምስት ዓመት በላይ ለተፈጸመ ለእያንዳንዱ አገልግሎት ዘመን 1.125 በመቶ ተጨምሮ ይታሰባል ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሰረት የሚወሰነው የአበል መጠን የመንግስት ሠራተኛው ፤ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊው ወይም የምክር ቤት አባሉ መጨረሻ ባገለገለባቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ ይከፈለው ከነበረው አማካይ ደመወዝ 70 በመቶ ሊበልጥ አይችልም ፡፡

21.<u>የአገልግሎት ዳረጎት</u>

1. ከአስር ዓመት ያነሰ አገልግሎት የፈጸመ የመንግስት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜው በመድረሱ ከስራ ሲሰናበት የአገልግሎት ዳረጎት ይከፈለዋል ፡፡
2. ከአንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያነሰ አገልግሎት ያለው የመንግስት ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል ከኃላፊነት ሲነሳ ዕድሜው 50 ዓመት ወይም በላይ ከሆነ የአገልግሎት ዳረጎት ይከፈለዋል ፡፡

22.<u>የአገልግሎት ዳረጎት መጠን</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 መሰረት የሚከፈለው ዳረጎት ፡-

1. የመከላከያ ሠራዊት ወይም የፖሊስ አባል ላልሆነ የመንግስት ሠራተኛ ከስራ ከተሰናበተበት ወር በፊት ይከፈለው የነበረው የ1.25 በመቶ ወር ደመወዙ በአገለገለበት ዓመት ቁጥር ተባዝቶ ይታሰባል ፡፡
2. ለመከላከያ ሠራዊት ወይም ለፖሊስ አባል ከስራ ከተሰናበተበት ወር በፊት ይከፈለው የነበረው የ1.65 በመቶ ወር ደመወዙ በአገለገለበት ዓመት ቁጥር ተባዝቶ ይታሰባል ፡፡
3. ለከፍተኛ የመንግስት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል ከኃላፊነት ከተነሳበት ወር በፊት ይከፈለው የነበረው የ1.25 በመቶ ወር ደመወዙ በአገለገለበት ዓመት ቁጥር ተባዝቶ ይታሰባል

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ስለጤና ጉድለት ጡረታ አበልና ዳረጎት</u>

23 <u>የጤና ጉድለት ጡረታ አበል</u>

1. ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ የመንግስት ሠራተኛ በጤና ጉድለት ምክንያት ደመወዝ የሚያስገኝ ማናቸውንም ስራ መስራት የማይችል በመሆኑ ከስራ ሲሰናበት የጤና ጉድለት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል ፡፡
2. ቢያንስ አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያገለገለ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል በጤና ጉድለት ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሣ የጤና ጉድለት የጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፡፡

24. <u>የጤና ጉድለት የጡረታ አበል መጠን</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 መሰረት የሚከፈለው የጤና ጉድለት ጡረታ አበል በአንቀጽ 20 መሰረት ይታሰባል፡፡

25. <u>የጤና ጉድለት ዳረጎት</u>

1. ከ10 ዓመት ያነሰ አገልግሎት የፈጸመ የመንግስት ሠራተኛ በጤና ጉድለት ምክንያት ለስራ ብቁ ባለመሆኑ ከስራ ሲሰናበት የጤና ጉድለት ዳረጎት ይከፈለዋል

2. ከአንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያነሰ አገልግሎት ያለው ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል በጤና ጉድለት ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሣ የጤና ጉድለት ዳረጎት ይከፈለዋል ፡፡

26. <u>የጤና ጉድለት ዳረጎት መጠን</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 መሰረት የሚከፈለው ዳረጎት በአንቀጽ 22 መሰረት ይታሰባል፡፡

27. <u>ስለ ጡረታ መዋጮ ተመላሽ</u>

1 .አንድ የመንግስት ሠራተኛ ፡-

ሀ/ ከ10 ዓመት ያላነሰና 20 ዓመት ያልሞላ አገልግሎት ፈጽሞ በራሱ ፈቃድ ስራውን ከለቀቀ ፤ወይም

ለ/ ከ20 ዓመት ያነሰ አገልግሎት ፈጽሞ በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ ምክንያት ከስራ ከተሰናበተ፤

የአሰሪውን ድርሻ ሳይጨምር ሠራተኛው ራሱ ባዋጣው መጠን ብቻ የጡረታ መዋጮ ይመለስለታል ፡፡

2. ከ10 ዓመት ያነሰ አገልግሎት ፈጽሞ በራሱ ፈቃድ ስራውን የለቀቀ የመንግስት ሠራተኛ ምንም ዓይነት ክፍያ አያገኝም ፡፡

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>ስለጉዳት ጡረታ አበልና ዳረጎት</u>

<u>ትርጓሜ</u>

1. ‹‹በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት›› ማለት በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው፡፡
2. ‹‹በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ ›› ማለት የመንግስት ሠራተኛው መደበኛ ስራውን በማከናወን ላይ እንዳለ ወይም ከስራ ጋር በተያያዘ ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ የተፈጥሮ ተግባር ላይ በድንገት የሚደርስ ጉዳት ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

   ሀ/ የመንግስት ሠራተኛው ከመደበኛ ስራው ወይም መደበኛ ስራ ቦታው ወይም ሰዓት ውጪ ስልጣኑ በሚፈቅድለት የስራ ኃላፊ የተሰጠውን ትዕዛዝ በመፈጸም ላይ እያለ የደረሰን ጉዳት፤

ለ/ ስልጣኑ በሚፈቅድለት የስራ ኃላፊ የተሰጠ ትዕዛዝ ባይኖርም የመንግስት ሠራተኛው በመንግስት መስሪያ ቤቱ ውስጥ የደረሰን ድንገተኛ አደጋ ወይም ጥፋት ለመከላከል በስራ ሰዓት ወይም ከስራ ሰዓት ወጪ በሚፈጽመው ተግባር ምክንያት የደረሰን ጉዳት፤

ሐ/ የመንግስት ሠራተኛው ወደ ስራ ቦታው ወይም ከስራ ቦታው የመንግስት መስሪያ ቤቱ ለመንግስት ሠራተኞች አገልግሎት እንዲሰጥ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት ወይም የመንግስት መስሪያ ቤቱ ለዚህ ተግባር በተከራየውና በግልጽ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት በመጓዝ ላይ በነበረበት ጊዜ የደረሰን ጉዳት፤

መ/ የመንግስት ሠራተኛው ከስራው ጋር በተያያዘ ግዴታ የተነሣ ከስራው በፊት ወይም በኂላ ወይም ስራው ለጊዜው ተቋርጦ በነበረበት ጊዜ በስራው ቦታ ወይም መስሪያ ቤቱ ግቢ ውስጥ በመገኘት የደረሰበትን ማንኛውንም ጉዳት ፤

ሠ/ የመንግስት ሠራተኛው ስራውን በመከናወን ላይ ባለበት ጊዜ በመንግስት መስሪያ ቤቱ ወይም በሦስተኛ ወገን ድርጊት ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት ።

3. ‹‹በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ›› ማለት የመንግስት ሠራተኛው ከሚሰራው የስራ ዓይነት ወይም ስራውን ከሚያከናውንበት አካባቢ የተነሳ በሽታውን ለሚያስከትሉ ሁኔታዎች ተጋልጦ በመቆየቱ ምክንያት የደረሰ የጤና መታወክ ሲሆን ስራን በሚያከናንበት ቦታ የሚዛመቱና የሚይዙ ነዋሪ ወይም ተላላፊ በሽታዎችን አይጨምርም ።
4. ‹‹መደበኛ ስራ ›› ማለት የመንግስት ሠራተኛው በተሰጠው ኃላፊነት ወይም የስራ ውል መሰረት የሚያከናውነው ተግባር ነው ።
5. ‹‹መደበኛ የስራ ቦታ ›› ማለት የመንግስት ሠራተኛው የመስሪያ ቤቱን ስራ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የሚያከናውንበት ሥፍራ ነው ።

29 .<u>በራስ ላይ ጉዳት ስለማድረስ</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 የተመለከተው ተቀባይነት የሚኖረው የመንግስት ሠራተኛው ጉዳቱ እንዲደርስበት ሆነ ብሎ ያላደረገው ሲሆን ነው ። በተለይም ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንቶች የደረሰ ጉዳት የመንግስት ሠራተኛው በራሱ ላይ ሆን ብሎ ያደረሰው ጉዳት ሆኖ ይቆጠራል ፡-

1. በመንግስት መስሪያ ቤቱ አስቀድሞ በግልጽ የተሰጡትን የደህንነት መጠበቂያ መመሪያዎች መጣስ ወይም የአደጋ መከላከያ ደንቦችን መተላለፍ ፤ ወይም

2. አካሉን ወይም አእምሮውን በሚገባ ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ወይም በአደንዘዥ ዕፅ ሰክሮ በስራ ላይ በመገኘት ፤የደረሰ ጉዳት ፡

30. <u>በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታና የአካል ጉዳት መጠን ሠንጠረዥ</u>

1.ኤጀንሲው አግባብ ካለው አካል ጋር በመመካከር ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ፡-

ሀ/ የአካል ጉዳት መጠን ፤

ለ/ እያንዳንዱን በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታን በሚመለከት ፡-

1/ የበሽታውን ምልክቶች፤

2/ ለበሽታው መነሻ ይሆናል ተብሎ የሚታመነውን የስራ ዓይነት ወይም አካባቢ፤

3/ በሽታውን ለሚያሲዘው የስራ ሁኔታ ለመጋለጥ የሚያስፈልገውን አነስተኛ ጊዜ፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የወጣው ሰንጠረዥ እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው ይሻሻላል፡፡

31. <u>ግምት</u>

1. ከስራ ቦታ ወይም ከስራው ዓይነት ጋር የተያያዘ በሰንጠረዡ ውስጥ የተመለከተ በሽታ በተጠቀሰው የስራ ቦታ ወይም የስራ ዓይነት ላይ የተሰማራን የመንግስት ሰራተኛ የያዘው እንደሆነ በሽታው በስራ ምክንያት እንደመጣ ይቆጠራል ፡፡

2.በስራ ምክንያት በሚመጣ በሽታ ተይዞ የዳነ የመንግስት ሠራተኛ በሰንጠረዡ ውስጥ በበሽታው አንጻር በተመለከተው የስራ ዓይነት ላይ ተመድቦ መስራት በመቀጠሉ በዚያው በሽታ እንደገና ቢያዝ አዲስ በሽታ እንደያዘው ይቆጠራል ፡፡

3.በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተው ቢኖርም በመደበኛ ስራው ምክንያት ተላላፊ ወይም ነዋሪ በሽታዎችን በማጥፋት ላይ የተሰማራ የመንግስት ሠራተኛ በዚሁ በሽታ ከተያዘ በስራ ምክንያት የመጣ በሽታ እንደያዘው ይቆጠራል ፡፡.

32. <u>ማስረጃ ማቅረብ ስለመቻሉ</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30 መሰረት በሚወጣው ሠንጠረዥ ውስጥ ያልተመለከተ በሽታ በስራ ምክንያት የመጣ መሆኑን ፣ እንዲሁም በሰንጠረዡ ውስጥ የተመለከተ በሽታ በአንጻሩ ከተመለከቱት ምልክቶች በተለየ ሁኔታ የተከሰተ መሆኑን ለማረጋገጥ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል ።

## 33. <u>አደጋን ስለማስታወቅ</u>

ከመከላከያ ሠራዊት አባል በስተቀር አንድ የመንግስት ሠራተኛ በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ የመንግስት መስሪያ ቤቱ አደጋው ከደረሰበት ቀን አንስቶ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለኤጀንሲው ማስታወቅ አለበት ። ይህ ባለመደረጉ በመንግስት ሠራተኛው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት መስሪያ ቤቱ ኃላፊ ይሆናል ።

## 34. <u>ስለ አካል ጉዳት መጠን አወሳሰን</u>

1. በስራ ምክንያት የሚመጣ ጉዳት መጠን የሚወሰነው ስልጣን በተሰጠው የህክምና ቦርድ ነው።
2. ማንኛውም የህክምና ቦርድ በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት መጠንን የሚተምነው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30 በተመለከተው ሠንጠረዥ መሰረት ይሆናል ።
3. ኤጀንሲው አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በአንድ የህክምና ቦርድ የተሰጠ ውሳኔ በሌላ የህክምና ቦርድ እንደገና እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል ።

## 35. <u>የጉዳት አበል</u>

በስራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ምክንያት ከ10 በመቶ ያላነሰ ሊድን የማይችል ጉዳት ለደረሰበት የመንግስት ሠራተኛ እንደሁኔታው የጉዳት ጡረታ አበል ወይም የጉዳት ዳረጎት ይከፈላል ።

## 36. <u>የጉዳት ጡረታ አበል</u>

አንድ የመንግስት ሠራተኛ በስራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ምክንያት ከ10 በመቶ ያላነሰ ሊድን የማይችል ጉዳት ደርሶበት ደመወዝ የሚያስገኝ ማናቸውም ሥራ መስራት የማይችል በመሆኑ ከስራ ሲሰናበት የጉዳት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል ።

## 37. <u>የጉዳት ጡረታ አበል መጠን</u>

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 መሰረት የሚከፈለው የጉዳት ጡረታ አበል መጠን የመንግስት ሠራተኛው ጉዳቱ ከደረሰበት ወር በፊት ያገኝ የነበረው የወር ደመወዝ 47 በመቶ ይሆናል ።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት አበል ሊከፈለው የሚችል የመንግስት ሰራተኛ በአገልግሎቱ ሊያገኝ የሚችለው አበል በጉዳት ሊያገኝ ከሚችለው የበለጠ ከሆነ የአገልግሎት ጡረታ አበል ይከፈለዋል ፡፡

38. <u>የጉዳት ዳረጎት</u>

1.አንድ የመንግስት ሠራተኛ ከ10 በመቶ ያላነሰ ከስራ የመጣ ጉዳት ደርሶበት ስራ ለመስራት የሚችል ከሆነ የጉዳት ዳረጎት ለአንድ ጊዜ ይከፈለዋል ፡፡

2. የመንግስት ሠራተኛው አግባብ ባለው ህግ ወይም ህብረት ስምምነት መሰረት በአሰሪው የጉዳት ካሣ ወይም የመድን ክፍያ የሚከፈለው ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው የጉዳት ዳረጎት አይከፈለውም ፡፡

39. <u>የጉዳት ዳረጎት መጠን</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚከፈለው የጉዳት ዳረጎት መጠን የመንግስት ሠራተኛው ጉዳት ከደረሰበት ወር በፊት ይከፈለው የነበረው የወር ደመወዙ 47 በመቶ በ60 ተባዝቶ የሚገኘው ሂሳብ በመንግስት ሰራተኛው ላይ በደረሰው ጉዳት መቶኛ ተባዝቶ ነው ፡፡

## <u>ክፍል ስምንት</u>

## <u>የተተኪዎች ጡረታ አበልና ዳረጎት</u>

40.<u>ጠቅላላ</u>

1. ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ፡-

ሀ/ የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ወይም የጉዳት ጡረታ አበልበመከፈል ላይ እያለ፤ወይም

ለ/ ቢያንስ 10 ዓመት አገልግሎ በስራ ላይ እያለ፤ወይም

ሐ/ በስራ ላይ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ፤ከሞተ ለተተኪዎቹ የጡረታ አበል ይከፈላል፡፡

2. ከ10 ዓመት ያነሰ አገልግሎት ያለው የመንግስት ሠራተኛ በስራ ላይ እያለ ከሞተ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3//ሀ/ እና/ለ/ ለተመለከቱት ተተኪዎች ዳረጎት ይከፈላቸዋል ፡፡

3. የሟች ተተኪዎች የሚባሉት የሚከተሉት ይሆናሉ፤

ሀ/ ሚስት ወይም ባል፤

ለ/ ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑ ልጆች ወይም አካል ጉዳተኛ ወይም አዕምሮ በሽተኛ ልጅ ሲሆን ዕድሜው ከ21 ዓመት በታች የሆነ፤

ሐ/ ልጃቸው ከመሞቱ በፊት ሙሉ በሙሉ ወይም በአብዛኛው በሚች ድጋፍ ይተዳደሩ የነበሩ ወላጆች ፡፡

41.<u>የሚች ሚስት ወይም ባል ጡረታ አበል</u>

1/ ለሚች ሚስት ወይም ባል የሚከፈለው የጡረታ አበል ሚች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል የነበረው የጡረታ አበል 50 በመቶ ይሆናል ፡፡

2/ የሚች ሚስት ወይም ባል የጡረታ አበል ተወስኖ በመቀበል ላይ እያለ ጋብቻ ከፈጸመች ወይም ከፈጸመ ፡-

ሀ/ ሚስት ዕድሜዋ ከ45 ዓመት በታች ከሆነ፤ ወይም

ለ/ባል ዕድሜው ከ50 ዓመት በታች ከሆነ ፤

ጋብቻ ከተፈጸመበት ቀን ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ በመከፈል ላይያለው የጡረታ አበል ይቋረጣል ፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ /2/ መሰረት መቋረጥ የሚገባውን የጡረታ አበል የተቀበለች ወይም የተቀበለ የሚች ሚስት ወይም ባል መልሶ የመክፈል ግዴታ አለባት ወይም አለበት

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ እና /3/ ድንጋጌዎች በአካል ጉዳተኛ ሚስት ወይም ባል ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም ፡፡

5/ ለሚች ሚስት ወይም ባል በዚህ አንቀጽ መሰረት ከአንድ በላይ የጡረታ አበል የሚከፈልበት ሁኔታ ሲያጋጥም አንዱና የሚበልጠው ብቻ ይከፈላል ፡፡

42.<u>የሚች ልጅ ጡረታ አበል</u>

1. ለሚች ልጅ የሚከፈለው የጡረታ አበል ሚች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል የነበረው የጡረታ አበል 20 በመቶ ይሆናል ፡፡
2. ሁለቱም ወላጆች ለሞቱበት ልጅ በዚህ አንቀጽ (1) መሰረት የሚከፈለው የጡረታ አበል 30 በመቶ ይሆናል ፡፡
3. የጡረታ አበል የሚከፈላቸው ወይም ሊከፈላቸው ይችሉ የነበሩ ሁለቱም ወላጆች የሞቱበት ልጅ ከእያንዳንዳቸው አበል 20 በመቶ ይከፈለዋል ፤ሆኖም የጡረታ አበሉ ድምር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ሊከፈል ከሚችለው ያነሰ አይሆንም ፡፡

43. <u>የወላጅ ጡረታ አበል</u>

ለሟች ወላጆች ለእያንዳንዳቸው የሚከፈለው የጡረታ አበል ሟች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል የነበረው የጡረታ አበል 15 በመቶ ይሆናል ፡፡ ሆኖም ከወላጆች ሌላ ተተኪ ከሌለ 20 በመቶ ይሆናል ፡፡

44. <u>የተተኪዎች ዳረጎት</u>

ለማንኛውም ተተኪ የሚከፈለው ዳረጎት መጠን ለሟች በዚህ አዋጅ መሰረት ሊከፈለው ይገባ ከነበረው ዳረጎት እንደአግባቡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 41/1/ ወይም አንቀጽ 42 በተወሰነው መቶኛ ተባዝቶ ይታሰባል ፡፡

45. <u>የተተኪዎች አበል ገደብ</u>

1.በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 41 እስከ አንቀጽ 44 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ለተተኪዎች የሚከፈለው አበል ድምር ሟች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል ከነበረው አበል 100 በመቶ /መቶ በመቶ/ ሊበልጥ አይችልም ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተተኪዎች ጡረታ አበል ከተስተካከለ በኋላ የተተኪዎች ብዛት ከቀነሰ የአበሉ መጠን እንደገና ይስተካከላል ፡፡

## <u>ክፍል ዘጠኝ</u>

## <u>አበልን የሚመለከቱ የወል ድንጋጌዎች</u>

46. <u>ለዝቅተኛ የጡረታ አበል መጠንና የአበል መሻሻል</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ኤጀንሲው በሚያቀርበው ጥናት መሰረት በየአምስት ዓመቱ ዝቅተኛ ወርሀዊ የጡረታ አበል መጠንና የጡረታ አበል ማስተካከያ ያደርጋል ፡፡

47. <u>የጡረታ አበል አከፋፈልና የመክፈያ ጊዜ</u>

1/ የጡረታ አበል የሚከፈለው በየወሩ ይሆናል ፡፡

2/ የአገልግሎት ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው የመንግስት ሠራተኛው በዕድሜ ለጡረታ ብቁ ከሆነበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው ፡፡

3/ የጤና ጉድለት ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው የመንግስት ሠራተኛው በጤና ጉድለት ምክንያት መስራት የማይችል መሆኑ በህክምና ቦርድ ከተረጋገጠበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው፡፡

4.የጉዳት ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው የመንግስት ሠራተኛው በጉዳት ምክንያት መስራት የማይችል መሆኑ በህክምና ቦርድ ከተረጋገጠበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው ፡፡

5. የተተኪዎች ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው ባለመብቱ ከሞተበት ቀጥሎ ካለው ወር መጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው፡፡

48. <u>የዳረጎት አከፋፈልና የመክፈያ ጊዜ</u>

1. ማንኛውም ዳረጎት የሚከፈለው በአንድ ጊዜ ነው

2. የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ዳረጎት ተከፋይ የሚሆነው የመንግስት ሠራተኛ ከስራ ከተሰናበተበት ቀጥሎ ባለው ወር የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ነው፡፡

3. የጉዳት ዳረጎት ተከፋይ የሚሆነው የመንግስት ሠራተኛው ላይ ጉዳት ስለመድረሱና መጠኑን የሚገልጽ ማስረጃ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ነው ፡፡

49. <u>የይርጋ ጊዜ</u>

1/ ማኛውም የውዝፍ ጡረታ አበል ወይም የዳረጎት ክፍያ ጥያቄ ከሦስት ዓመት በኋላ በይርጋ ይታገዳል ፡፡

2/ የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ጥያቄ ሠራተኛው የጡረታ መውጫ ዕድሜ ከሞላ ወይም ከሞተ ከሦስታ ዓመት በኋላ በይርጋ ይታገዳል ፡፡

3/ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በመብቱ መጠቀም ከሚችልበት ቀጥሎ ካለው ቀን አንስቶ ነው

4. በሚከተሉት ምክንያቶች የባከነ ጊዜ ለይርጋ አቆጣጠር አይታሰብም ፡-

ሀ/ ባለመብትነትን ለማረጋገጥ የተጀመረ የፍርድ ቤት ሥርዓት እስከሚጠናቀቅ የወሰደው ጊዜ፤

ለ/ ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት መረጃ የማስተላለፍ ግዴታውን በወቅቱ ባለመወጣቱ ያለፈው ጊዜ

ሐ/ ኤጀንሲው የቀረበለትን የክፍያ ጥያቄ መርምሮ ለመወሰን የወሰደው ጊዜ፡፡

50. <u>አበል የማግኘት መብትን ማስተላለፍ ስላለመቻሉ</u>

አበል የማግኘት መብት የዕዳ መያዣ ሊደረግ ወይም በውርስም ሆነ በሌላ በማናቸውም መንገድ ሊተላለፍ አይችልም ፡፡

51. <u>ስለአበል በሕግ መከበር</u>

በዚህ አዋጅ መሰረት የሚሰጥ አበል፡-

1. ለመንግስት ገቢ የሚሆን መቀጮ ፣ግብር ወይም ቀረጥ ለመክፈል፤ ወይም

2/ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ቀለብ የመስጠት ግዴታውን ለመወጣት፤በፍርድ ቤት ካልታዘዘ በስተቀር በሌላ ዕዳ ምክንያት አይከበርም።

## ክፍል አስር

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

52. የመብቶች ግንኙነት

1/ የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት በመንግስት መስሪያ ቤት በቋሚነት ከተቀጠረና ለጡረታ መውጫ ዕድሜ ያልደረሰ ከሆነ አዲሱ አገልግሎት ከቀድሞው አገልግሎቱ ጋር ተዳምሮ ይታሰብለታል ። ሆኖም እንደገና የታሰበው አበል ከቀድሞው አበል ያነሰ ከሆነ የቀድሞውን አበል የማግኘት አበል ይኖረዋል ።

2/ በዚህ አዋጅ ክፍል ስምንት የጠደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ባለመብት በዚህ አዋጅ መሰረት ከአንድ በላይ የጡረታ አበል የሚያገኝበት ሁኔታ ሲያጋጥም ሊከፈል የሚገባው የአበል መጠን ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይወሰናል ።

3/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከግል ወደ መንግስት ይዞታ በተዛወረ ድርጅት ድርጅቱ ከመዛወሩ በፊት ሲከፈል የነበረ ወርሀዊ የጡረታ አበል በዚህ አዋጅ መሰረት ተስተካክሎ ይከፈላል ።

4.ከ10 ዓመት ያላነሰ አገልግሎት ላላቸው ወይም ከአምስት አመት ያነሰ አገልግሎት ኖሯቸው አገልግሎታቸው ሲቋረጥ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ላይ ለደረሱ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎችና የምክር ቤት አባላት አበል አወሳሰን የመከላከያ ሠራዊት ወይም የፖሊስ አባል ያልሆኑ የመንግስት ሠራተኞችን የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ ።

5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 653/2001 አንቀጽ 55 መሰረት መብቶችና ጥቅሞቹ እንዲቋረጡ የተወሰነበት ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19/5 ወይም አንቀጽ 23/2/ መሰረት የሚከፈለው የጡረታ አበል ይቋረጣል ።

53. መረጃ የመስጠትና የመተባበር ግዴታ

1. ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት በዚህ አዋጅ ክፍል ሁለት ድንጋጌዎች መሰረት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ እያንዳንዱን የመንግስት ሠራተኛ የሚመለከቱ መረጃዎችና ማስረጃዎች ማሰባሰብ ፣ማጠናቀር፣ ማደራጀትና በኤጀንሲው በሚወሰነው ጊዜና ቅጽ መሰረት ለኤጀንሲው የማስተላለፍ ግዴታ አለበት ፡፡

2. ይህን አዋጅ በስራ ላይ ለማዋል እንዲቻል ማንኛውም ሰው የጽሁፍ ማስረጃ እንዲልክ ወይም ቀርቦ አስተያየትና መረጃ እንዲሰጥ በኤጀንሲው ሲጠየቅ የመስጠት ግዴታ አለበት ፡፡

3. የሚመለከታቸው አካላት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12(5) በሚሰጥ ውክልና መሰረት የጡረታ መዋጮ በመሰብሰብ ረገድ ከኤጀንሲው ጋር የመተባበር ግዴታ ይኖርባቸዋል

54. <u>የኤጀንሲው ውሳኔዎች</u>

1.በዚህ አዋጅ መሰረት ለሚሰጥ ለማናቸውም ዓይነት አበል ብቁ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መሟላታቸው የሚረጋገጠውና የአበሉ ዓይነትና መጠን የሚወሰነው በኤጀንሲው ይሆናል ፡፡

2. ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሰረት ውሳኔ የሚሰጠው የራሱን የመረጃ ማህደር ፣በዚህ አዋጅ አንቀጽ 53 መሰረት የሚተላለፉትን መረጃዎችና እንደአግባቡ ባለመብቱ የሚያቀርባቸውን ተጨማሪ ማስረጃዎች መሰረት በማድረግ ይሆናል ፡፡

3. በኤጀንሲው የመረጃ ማህደርና በቀረበለት ማስረጃ መካከል ልዩነት ቢፈጠር ተቀባይነት የሚኖረው ማስረጃ በኤጀንሲው ይወሰናል ፡፡

55. <u>ውሳኔን እንደገና ስለመመርመር</u>

1/ ቅሬታ ያለው ባለመብት በሚያቀርበው ጥያቄ ወይም በራሱ አነሳሽነት ኤጀንሲው ቀደም ብሎ የሰጠውን ውሳኔ እንደገና ለመመርመር ይችላል ፡፡

2/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 51 የተደነገገው ቢኖርም ኤጀንሲው ውሣኔውን እንደገና ሲመረምር የአበል መሰረዝ ፣መቀነስ ወይም መቋረጥ ሊያስከትል የሚችል በቂ ምክንያት ያገኘ እንደሆነ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ሊሰረዝ፣ ሊቀነስ ወይም ሊቋረጥ በሚገባው አበል መጠን ክፍያው ታግዶ እንዲቆይ ማድረግ ይችላል ፡፡

3/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 51 ድንጋጌ ቢኖርም እንደገና በተደረገው ምርመራ የጡረታ አበል እንዲቀነስ ኤጀንሲው ከወሰነ ወይም ከዚህ አዋጅ ድንጋጌ ውጪ ያለ አግባብ

የጡረታ አበል ከተከፈለ ኤጀንሲው ከባለመብቱ የጡረታ አበል ላይ እየቀነሰ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል ፡፡

56 <u>ስለይግባኝ</u>

1.ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 54 ወይም አንቀጽ 55 መሰረት በሰጠው ውሰኔ ቅር የጠሰኝ ማንኛውም ባለመብት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 57 ለተቋቋመው የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ይግባኝ የማቅረብ መብት ይኖረዋል ፡፡

2. የይግባኝ አቤቱታ ለጉባኤው መቅረብ የሚችለው ይግባኝ በሚባልበት ጉዳይ ላይ ውሳኔ በተሰጠ እስከ አንድ ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

3. ጉባዔው የቀረበለትን የይግባኝ አቤቱታ ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና አዋጁን ለማስፈጸም ከወጡ ደንቦችና መመሪያዎች አንጻር መርምሮ የኤጀንሲውን ውሳኔ መለወጥ ማሻሻል ወይም ማጽናት ይችላል ፡፡

4. ጉባዔው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ መሰረት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡ ሆኖም የጉባዔው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለው ብሎ የሚያምን ተከራካሪ ወገን ውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የማቅረብ መብት ይኖረዋል ፡፡

57. <u>የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ</u>

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 56 መሰረት የሚቀርቡ ይግባኞችን እየመረመረ ውሳኔ የሚሰጥ የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል ፡፡

2/ የጉባኤው አደረጃጀትና የአባላት አሰያየም በመንግስት ይወሰናል ፡፡

3/ ከጉባኤው አባላት አብዛኞቹ በጉባኤው ስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባዔ ይሆናል ፡፡

4/ የጉባዔው ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው በተገኙ አባላት በአብዛኛው ድምጽ ሲደገፍ ነው፤ሆኖም ድምጽ እኩል ለእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል ፡፡

5/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ጉባዔው የራሱን የአሰራር ስርአት ደንብ ሊያወጣ ይችላል ፡፡

58. <u>ከግብር ነጻ ስለመሆን</u>

በዚህ አዋጅ መሰረት በሚከፍል የጡረታ አበል በሚሰበሰብ የጡረታ መዋጮ እና ከጡረታ ፈንድ ኢንቬስትመንት በሚገኝ ትርፍ ላይ ግብር አይከፈልም ።

59. <u>*የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች*</u>

1/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ለተፈጠሩ ህጋዊ ሁኔታዎች ቀደም ሲል ሲሰራባቸው የነበሩ ሕጎችና መመሪያዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ ።

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 እና አንቀጽ 11 መሰረት በወር ደመወዝ ላይ ተመስርቶ የሚሰበሰበው የጡረታ ፈንድ መዋጮ ፦

ሀ/ ከመንግስት ሠራተኞች ይህ አዋጅ ከሚፀናበት ቀን አንስቶ ለአንድ አመት 5 በመቶ ከሁለተኛ ዓመት ጀምሮ 6 በመቶ እና ከሦስተኛው ዓመት ጀምሮ 7 በመቶ ይሆናል ።

ለ/ የሲቪል መንግስታዊ አገልግሎት ጡረታ ፈንድን በሚመለከት ከመንግስት መስሪያ ቤቶች ይህ አዋጅ ከሚፀናበት ቀን አንስቶ ለአንድ አመት 7 በመቶ ከሁለተኛ ዓመት ጀምሮ 8 በመቶ ከሦስተኛ ዓመት ጀምሮ 9 በመቶ እና ከአራተኛው ዓመት ጀምሮ 11 በመቶ ይሆናል

ሐ/ የወታደራዊና የፖሊስ አገልግሎት ጡረታ ፈንድን በሚመለከት ይህ አዋጅ ከሚፀናበት ቀን አንስቶ ለአንድ ዓመት 18 በመቶ ከሁለተኛ ዓመት ጀምሮ 20 በመቶ ከሦስተኛ ዓመት ጀምሮ 22 በመቶ እና ከአራተኛው ዓመት ጀምሮ 25 በመቶ ይሆናል፡፡

3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20/1/ እና አንቀጽ 24 መሰረት ለሚደረገው የአገልግሎት ጡረታ አበልና የጤና ጉድለት ጡረታ አበል ስሌት የሚገለግለው መቶኛ ፦

ሀ/ የመከላከያ ሠራዊት ወይም የፖሊስ አባል ያልሆኑ የመንግስት ሠራተኞችን በሚመለከት ይህ አዋጅ ከሚፀናበት ቀን አንስቶ ለአንድ ዓመት 1.15 በመቶ ለሁለተኛው ዓመት 1.19 በመቶ ለሦስተኛው ዓመት 1.22 በመቶ እና ከአራተኛው ዓመት ጀምሮ 1.25 በመቶ ይሆናል፡፡

ለ/ የመከላከያ ሠራዊት ወይም የፖሊስ አባልን በሚመለከት ይህ አዋጅ ከሚፀናበት ቀን አንስቶ ለአንድ ዓመት 1.53 በመቶ ለሁለተኛ

ዓመት 1.58 በመቶ ለሦስተኛው ዓመት 1.62 በመቶ እና ከአራተኛው ዓመት ጀምሮ 1.65 በመቶ ይሆናል ፡፡

4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 እና አንቀጽ 26 መሰረት ለሚደረገው የአገልግሎት ጡረታ ዳረጎትና የጤና ጉድለት ጡረታ ዳረጎት ስሌት የሚያገለግለው የደመወዝ መጠን ፡-

ሀ/ የመከላከያ ሠራዊት ወይም የፖሊስ አባል ያልሆኑ የመንግስት ሠራተኞችን በሚመለከት ይህ አዋጅ ከሚጸናበት ቀን አንስቶ ለአንድ ዓመት 1.15 በመቶ ለሁለተኛ ዓመት 1.19 በመቶ ለሦስተኛው ዓመት 1.22 በመቶ እና ከአራተኛው ዓመት ጀምሮ 1.25 በመቶ ይሆናል ፡፡

ለ/ የመከላከያ ሠራዊት ወይም የፖሊስ አባልን በሚመለከት ይህ አዋጅ ከሚጸናበት ቀን አንስቶ ለአንድ ዓመት የ1.53 ወር ደመወዝ ለሁለተኛ ዓመት የ1.58 ወር ደመወዝ ለሦስተኛው ዓመት የ1.62 ወር ደመወዝ እና ከአራተኛው ዓመት ጀምሮ የ1.65 ወር ደመወዝ ይሆናል ፡፡

5 / ከመንግስት ወደ ግል ከተዛወሩት ድርጅቶች ጋር የተዛወሩ የመንግስት ሠራተኞች ይህ አዋጅ ከሚጸናበት ጊዜ ጀምሮ ለግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ መዋጮ ይከፍላሉ ፡፡ ሆኖም የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ዐቅዱ የጡረታ አበል መወሰን ከመጀመሩ በፊት በጡረታ የሚገለሉ ከሆነ አሰሪውና ሠራተኛው የከፈሉት የጡረታ መዋጮ ለመንግስት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ እንዲዛወር ተደርጎ የጡረታ አበል ይወሰናል ፡፡

6/ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ 30 የተጠቀሰውን የአካል ጉዳት መወሰኛ ሰንጠረዥ እስከሚያወጣ ድረስ የህክምና ቦርዶች የሚከተሉት አሰራር ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል ፡፡

60. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል ፡፡

3. ኤጀንሲው ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል ፡፡

61. <u>ቅጣት</u>

የያዘውን ማስረጃ በዚህ አዋጅ መሰረት ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም የዚህን አዋጅ ድንጋጌ አፈጻጸም የሚያሰናክል ተግባር የፈጸመ ማንኛውም ሰው በወንጀል ህግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራትና እስከ ብር10 ሺህ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

62. <u>የተሻሩና ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች</u>

1. የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል ፡-

ሀ/ የመንግስት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ 345/1995 (እንደተሻሻለ)

ለ/ የመንግስት ልማት ድርጅቶችን ግል ለማዛወር የወጣው አዋጅ ቁጥር 146/1991 አንቀጽ 12 እና የጡረታ ሽፋንን የሚመለከተው አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ፤

ሐ/ ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግስት መሪዎች፣ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች ፣ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች መብትና ጥቅሞች አዋጅ ቁጥር 653/2001 አንቀጽ 12 እና 21 ፡፡

2. ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ማናቸውም ህጎች ወይም የአሰራር ልምዶች ይህን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም ፡፡

63. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ 17 ቀን 2003 ዓ.ም

ግርማ ወ/ጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት